widu

# ዊዱ ዶት አፍሪካ በኢትዮጵያ

ከዳያስፓራ ጋር በመተባበር የሚደረግ የገንዘብ ድጋፍ እና የስልጠና እገዛ ሲሆን ይህንንም በበየነመረብ አማካኝነት ያስተዋውቃል።



## ተግዳሮት

በተለያዩ የአፍሪካ አገራት የስራ ዕድል መኖር ለዕድገት እና መረጋጋት በጣም ወሳኝ ነው። በዚህ ረገድ በአፍሪካ የሚገኙ ብዙ የስራ ፈጣሪዎች አዳዲስ የስራ ዕድል የመፍጠር አቅም አላቸው። ነገር ግን ይህንን አቅም ከዚህ ቀደም በንግድ እና በሌሎች እንቅስቃሴዎች ተግባር ላይ ያዋሉት በጣም ጥቂቶች ናቸው። አንዳንዴ ሙሉ አቅማቸውን ለመጠቀም በጣም ይቸገራሉ። ይህንን ችግር ለመቅረፍ ደግሞ ከዳያስፓራ ጋር መተባበር ሁነኛ መፍቴሄ ነው:: እንደ ዓለም ባንክ ግምታዊ መረጃ በጀርመን የሚኖሩ አፍሪካውያን በዓመት እስከ 1. 5 ቢልዮን ዩሮ ወደ ሃገራቸው ይልካሉ። ከዚህ ውስጥ በጣም ውስን መጠን ብቻ በንግድ እና መሰል እንቅስቃሴዎች ይውላል። በመሆኑም ተግባር ላይ ያልዋለውን እምቅ አቅምን ለመጠቀም፣ ዳያስፓራ ለስራ ፈጠራ በዕውቀት ሽግግር እና በገንዘብ ድጋፍ እዲያግዝ ለማሳተፍ ምቹ ሁኔታ አለ።

## አካሄዳችን

በ2030 አፍሪካ-አውሮጳ የጋራ ራዕይ መሰረት በማድረግ፤ ለዘላቂ ስራ ዕድል ፈጠራ እንዲያግዝ እና ዲጅታል ለውጥን ለማምጣት ዊዱ ዶት አፍሪካ የንግዱን ዘርፍ ማገዝ ላይ ትኩረት አድርጓል። ይህ ፕሮጀክት በጥምር የገንዘብ እና የስልጠና ድጋፍ የስራ ፈጣሪዎች ያላቸውን እምቅ አቅማቸውን እንዲጠቀሙ ብሎም ወደ ስራ ዕድል እንዲፈጥሩ እና ገቢ ማመንጨት እንዲችሉ ይረዳቸዋል። ይህንኑ ለማሳካት ዊዱ ዶት አፍሪካ አውሮፓ ከሚኖሩ የኢትዮጵያውያን ዳያስፓራ ጋር በትብብር ይሰራል። ስለሆነም ኢትዮጵያዊው ዳያስፖራ ሀገር ቤት የሚኖሩ ዘመዶቻቸውን እና ቤተሰቦቻቸውን በፕሮግራሙ ላይ እዲሳተፉ በመጋበዝ እንዲሁም በአኳዝ የተደገፈ የመጀመሪያውን አዋጭ ነው ብለው የሚያምኑትን የንግድ ዘርፍ በአንድነት ይመርጣሉ። ከዚህ በመቀጠል የዳያስፓራ አጋዥ እና ሀገር ቤት ያለው የስራ ፈጣሪ በዊዱ ዶት አፍሪካ በበይነመረብ ላይ የፕሮጅክት ሀሳባቸውን በማካተት የጋራ ኢንቨስትመ ንታቸውንም በእኩል መጠን ያዋጣሉ። ዊዱ ዶት አፍሪካ በኢትዮጵያ የተቋቋመው እ. አ. አ. በህዳር ወር 2021 ሲሆን ይህንን ፕሮጀክት የጀርመን ፌዴራላዊ የኢኮኖሚ ትብብር እና ልማት ሚኒስቴር (ቢ ኤም ዜድ)ን በመወከል የሚተገብረው የጀርመን አለም አቀፍ ትብብር ለጋራ ዕድገት (ጂ አይ ዜድ) ግምብኤች ነው። በአሁኑ ጊዜ ዊዱ ዶት አፍሪካ ኢትዮጵያን ጨምሮ በካሜሩን፣ በጋና፣ በኬንያ፣ በቶጎ እና በቱኒዝያ ይገኛል።

## ውጤቶቻችን

በኢትዮጵያ ከተመሰረተበት ጊዜ አንስቶ ዊዱ ዶት አፍሪካ በሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እድገት እና ስራ ፈጠራ ዙሪያ ውጤታማ አስተዋጽዎ አድርጓል። በበየነመረብ/ አማካኝነት ዳያስፓራ ከስራ ፈጣሪዎች ጋር አንድ ላይ በመሆን ከ196,000 ዩሮ በላይ የግል ኢንቨስትመንት በጥቃቅን እና አነስተኛ ንግድ ዘርፍ፣ ዊዱ ዶት አፍሪካ እንደ አንድ ተባባሪ ማበርከት ችሏል።

ዊዱ ከ **297,500 Euros** ዩሮ በላይ በድጋፍ መልክ ከፍሏል። ከ **224** በላይ ጥቃቅን እና አነስተኛ ዘርፎች ተደግፏል።

ከዚያ ውስጥ **63%** በሴቶች የሚመሩ ናቸው።

የዊዱ ዶት አፍሪካ ድጋፍ ከ**261** በላይ አዳዲስ እና ቋሚ ስራዎችን አፍርቷል።

በዚህ ተግባር በተለይም ሴቶች ተጠቃሚ ሆነዋል።

ከስራዎቹ መካከል **66%** የተያዙት በሴቶች ነው።

ከ **466** የግል ስልጠናዎች ቧኋላ፣ **94%** ተሳታፊዎች የወሰዷቸው የግል ስልጠናዎች የንግድ ክህሎታቸውን እንዲያሻሽሉ አግዟቸዋል።

ባአጠቃላይ እ. አ. አ ከጥቅምት 2019 ጀምሮ ዊዱ ዶት አፍሪካ ከ **4,980** በላይ የንግድ ዘርፎችን በስድስት ተሳታፊ በሆኑ ሀገሮች ድጋፍ ያደረገ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ

**46%** የሚመረው በሴቶች ነው።

በተጨማሪ ዊዱ ዶት አፍሪካ ከ **9,315** ቋሚ ስራዎች እንዲፈጠሩ አግዟል ( **50%** በሴቶች የተያዙ ናቸው)።

የ2 ዓመት አትኩሮት የተሞላበት፣ የውጤታማነት ግምገማ መሰረት በማድረግ ዊዱ ዶት አፍሪካ ስራ ፈጣራ እና ገቢን በማሳደግ ረገድ ውጤታመ መሆኑን አስመስክሯል።

german cooperation
DEUTSCHE ZUSAMMENARBEIT

Implemented by

giz Deutsche Gesellschaft für Internationale Zusammenarbeit (GIZ) GmbH

**ዊዱ ዶት አፍሪካ በአፍሪካ ላሉ ለአነስተኛ የንግድ ዘርፎች የሚሰጣቸው የድጋፍ አይነቶች**

ዊዱ ዶት አፍሪካ ሁኔታዎችን ታሳቢ ያደረግ የድጋፍ አይነቶችን እንዲሁም በቀላሉ ሊያድጉ የሚችሉ ጥቃቅን እና አነስተኛ የንግድ ዘርፎችን መደገፍ ላይ ትኩረት ያደረገ ነው። በኢትዮጵያ፣ ዊዱ ዶት አፍሪካ ስራ ፈጣሪዎችን በመደበኛ ዊዱ ድጋፍ እና ጊዜያዊ ድጋፎች ላይ መሰረት አድርጎ እገዛ ያደርጋል።

### መደበኛ የዊዱ ድጋፍ

ይህ ፕሮግራም የዊዱ የመጀምሪያ የድጋፍ አይነት ነው። በዚህም በዳያስፓራ ለሚደገፉ ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ዊዱ የገንዘብ ድጋፍ ይሰጣል። የገንዘብ ድጋፍ መጠን እስከ 2, 500 ዩሮ ሲሆን፣ ዕድሉም ለሁሉም አይነት የንግድ ዘርፍ ክፍት ነው።

### ጊዜያዊ የዊዱ ድጋፍ

ይህ የገንዘብ ድጋፍ በሀገር ውስጥ ላሉ ለስራ ፈጣሪዎች ክፍት ነው። ጊዜያዊ የገንዘብ ድጋፍ በተወሰኑ ርዕሰ ጉዳዮች የተገደበ ሆኖ የበለጠ ጠቀሜታ አለው ተብሎ በሚታመነው የኢኮኖሚ ዘርፍ የተወሰነ ሲሆን ድጋፉም እስከ 5,000 ዩሮ ነው። እ. አ. አ በመስከረም 2022 ዊዱ ለመጀመሪያ ጊዜ በምግብ ዋሰትና ዘርፍ ዙሪያ ዕድሉን ክፍት አድርጓል። በዚህ ዘርፍ ዊዱ ዘላቂ ለሆኑ የንግድ ሀሳቦች ድጋፍ አድርጓል። በሌሎች ሀገሮች ደግሞ በአዳዲስ ርዕሶች ዕድሉ ክፍት ሆኗል (በአሩንጓዴ ልማት ዘርፍ፣ በዲጅታላይዜሽን፣ በሴቶች)።

## የዊዱ አፍሪካ እንቅስቃሴዎች

ግቡን ለማሳካት ዊዱ አፍሪካ በበየነመረብ ሁሉን አቀፍነትን፣ ተጠያቂነትን እና ግልጽነትን የሚያበረታቱ ዘዴዎችን ቀይሷል። ይህ አካሄድ በኦንላይን እና ኦፍላይን የፕሮጀክት ፕሮፓዛሎችን እና ውጤቶችን በጥራትና እና በውጤታማነት ማሰባሰብንም ያካተተ ነው። ነገሮችን በበየነመረብ ለመስራት መቻላችን ከፍ ባለ ደረጃ እና ሰፊ ቁጥር ያላቸውን የስራ ፈጣሪዎችን በኢትዮጵያ ብሎም በአፍሪካ ደረጃ ለማዳረስ እንድንችል አስችሎናል።

የስራ ፈጣሪዎቹ የንግድ እንቅስቃሴዎቻቸውን በውጤታማነት ለማንቀሳቀስ እንዲያስችላቸው እና በተገቢው መልኩ ለማቀድ እንዲያስችላቸው ዘንድ የዊዱ ፕሮጀክት በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ የንግድ ሀሳብ አማካሪዎችን በመመደብ ክትትል እና ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል። በመሆኑም የጂ አይ ዜድ ፕሮጀክት የንግድ ሀሳብ አመንጪዎች በሚያስፈልጋቸው ክህሎት ራሳቸውን እንዲያበቁ ያደርጋል።



> **ይህ የገንዘብ ድጋፍ ህልሜን ዕውን እንዳደርግ ረድቶኛል። በአሁኑ ሰዓት ባለሙያዎችን በመቅጠር ምርት እያመረትኩኝ ሲሆን ለሌሎችም የስራ ዕድል አስገኝቷል::**

**አዜብ ተመስገን፣ ሉላ ዲዛይን (የስፌት ሱቅ)**


## ስለህትመት

**አሳታሚው:-**
የጀርመን አለም አቀፍ ትብብር ለጋራ ዕድገት (ጂ አይ ዜድ) ግምብኤች

ቢሮዎቹ የሚገኙባቸው ቦታዎች:-

ቦን እና ኤሽቦርን በጀርመን ሀገር ሲሆን

በኢትዮጵያ ቢሮው የሚገኝበት ቦታ

ካሳንቺስ፣ ቂርቆስ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 08፣ አዲስ አበባ

ኢሜይል:- ethiopia@widu.africa

በየነመረብ አድራሻ:- www.widu.africa

በየነመረብ አድራሻ:- www.giz.de

www.widu.africa

**ፕሮግራም/የፕሮጀክቱ ገለጻ:-**
በአፍሪካ ውስጥ የዳያስፓራን የገንዘብ ድጋፍ በመጠቀም በግሉ ዘርፍ የንግድ ሀሳብን ማበረታታት

**አሳታሚ/የሚመለከተው/ኤድቴር**

**ወልፍራም ዙንዘር (የፕሮጅክት ኋላፊ/**

**ዲዛይን/ሌይአውት፡**

**ዳይመንድ ሚዲያ ጊምቢኤች፣ ኒውንክሪሼን-ሴልሻይድ**

**ዩአርኤል ሊንክስ:-**

በዚህ ህትመት ከተቋም ውጭ በሆኑ በየነመረብ አማካኝነት ለታተሙ ነገሮች የሚመለከተው አሳታሚ ኋላፍነት ይወስዳል። ለመሰል የህትመት ይዘቶች ጂ አይ ዜድ አይመለከተውም።

የጀርመን ፌዴራላዊ የኢኮኖሚ ትብብር እና ልማት ሚኒስቴር (ቢኤም ዚድ)ን በመወከል

ለዚህ ህትመት ጂ አይ ዜድ ኋላፍነቱን ይወስዳል።

ኤሽቦርን 2023